# ደህና ሰንብት አበጀ

ተፈጥሮም: የራሱን: ሂደት: እድገቱን: እየጠበቀ፣
ያልታሰበ: እየፈጠረ: ገና: በጉዞ: ላይ: ያለውን: በድንገት: እየነጠቀ።
ያልተጠራበት: እየገባ: የሚያወቀውን: ቤት: እየከፈተ፣
ዛሬ: ገና: ድል: መቻ: ጀግናውን: ይዞ: ተካተተ።

ምንድነው: ሞት? ወንድሞች: መተንፈስ: ማቆም: ሕይወት: ማጣት!!!!!
ከመሃል: ጠፍቶ: መቅረት: መሰወር: ለዘላለም: መረሳሳት?
እንዲያ: ከሆነስ: አልሰሚም ፣
በጭራሽ; ግቡን: አልመታም ።
እጁን: ቢይዘው: ብቻውን: አግኝቶት: ከመንገድ: ላይ፣
ስሙንስ: አይቀብረውም: ታሪኩ: ሕያው: ነው ከሞት በላይ።

እናም: አንቀበልም: ሞትህን: የሞተስ: ታሪክ: ያልሰራ፣
እኛ: አናወራም: መቀበርህን: የሚቀበር: በተግባሩ: የማይኮራ።
በምግባሩ: የማይተማመን: ባደረገው: ሁሉ: የሚያፍር ፣
በተናገረው: የሚጸጸት: አንገቱን: የሚያቀረቅር፣
ያንተ: የሚያኮራ: ነው: አበጀ: በሕይወት: ሳለህ: ሳንናገር: በሞትህ:
ሳልስት: እንመስክር።

ለሕዝብ: መቆምን: መርጠህ: የግል: ጥቅምህን: ኋላ: ብለህ፣
ከላብ: አደሩ: አብረህ: ከአርሶ: አደሩ: ተቀላቅለህ ፣
እንደሌላው: ሳትመጻደቅ: እንዲህ: እኮ: ነበርኩ: ብለህ፣
በአላማህ: ሳትዋዥቅ: በእምነትህ: ሳትደራደር፣
ባልመሰለህ: ፍርድ: ላይ: ባለመስማማትህ: ሳታፍር።

ምነው? ዛሬ: ታዲያ: ጌድ: አበጀ: ገና: ደፍርሱ: ሳይጠሩ፣
የተንከራተትክበት: ሜዳ: አቀበት: አንተን: መሰል: ሳያፈራ፣
ወገብህ: ገና: ሳይጠና: መንገድ: የጎዳው: እግርህ: ሳያገግም ፣
በሩጫ: ላይ: እንዳለህ: በድንገት: እንዲህ: ታዘግም ።
በሰላሙም: በትግሉም: ሁሌ: ታጥቀህ: እንዳልነበር፣
ዛሬ: ትጥቅህን: ትፈታው: መንገድ: ጥለኸው: ትቀበር።

እኔ: አላምንም: ይኸን: ለሰውም: እንዳትነግሩ፤
ሞቷል: ሲባል: የኖረ: ሰው: አለ: ሲባል: ልትቀብሩ?

አብረን: ስንኖር: እስከ: ዛሬ: ያላወቅሁት: ቅር: ያሰኘኝ፤
ኢትዮጵያዊነትህን: እንጂ: አማራ: መሆንክን: ሳትነግረኝ።

ደህና፡ ሰንብት፡ ኮሎኔል፡ አለማየሁ፡ እንዳለቃ፡ ሰላምታ፡ ልስጥህ፣
ደህና፡ ክረም፡ ጌድ፡ አበጀ፡ እንደታጋይ፡ ልሰናበትህ፣
ለታጋይ፡ አያለቅሱማ፡ ይላሉና፡ እኔም፡ አላለቅስልህ፣
እንደጌደኛ፡ ሆኜ፡ ግን፡ መጎዳቴን፡ ልግለጽልህ።

ተኮላ፡ መኮንን
November 10th 2000